# ወልቃይት ፀገዴ የማን መሬት ?

July 23, 2016

**አብርሃም በየነ**

ሞት ለሰው ልጆች ፀጋም ዕዳም የሚሆንበት ጊዜ አለው። ዜጎች መብታቸው ሲደፈር፣ ነፃነታቸው ሲገፈፍ፤ ማንነታቸው ሲፋቅና የመኖራቸው ህልውና በሞት ጥላ ስር ሲወድቅ ሞት ዕዳውን ያከብድባቸዋል። የክፍያውንም ዋጋ በሕይወት ይመነዝረውና መተኪያ የሌለውን ሕይወት በሞት ወለድ አገድ ያስይዘዋል። ህዝብም የታገቱትን መብቶቹን ለማስፈታት ሞትን ይኖሩታል እንጂ አይሞቱትም ብሎ ይንቀሳቀሳል። ሰው የተፈጠረው ለመሞት ነውና ሞትን ሙቶ ሊያቸንፈው ዕምቢኝ ለሀገሬ ሲል በሞት ላይ ያምፃል። ብሎም ጅግና ይፀነሳል። ሰማዕት ይወለዳል። ህዝብም ከመቃብር በላይ የሚውል ስም በደሙ ጽፎ ለማለፍ ሆ ብሎ ይነሳል።

የተቀሰቀሰው አመጽም መተኪያ የሌለውን ሕይወት ለመብትና ለሀገር ቤዛ በማድረግ ፀጋነቱን በህዝብ ሥነ-ልቦና ውስጥ ስርፀት እንዲያገኝ ያደርገዋል። ብሎም የሞት አስፈሪነት የጧት ጤዛ ወደ መሆን ይሸጋገርና ሞትን መሞት ሳይሆን ሞትን እየሞቱ መኖር የህዝብ ባህል ሆኖ ነጥሮ ይወጣል። ሞትን ይኖሩታል እንጂ አይሞቱትም እንዲሉም እንደ ፍልስጤሞች፣ እንደ አፍጋኖችና እንደ ጎንደሮች ሞትን ንቆ መኖር ይለመዳል። እናም የታገተው መብት እስኪፈታ፤ የተነጠቀው ነጻነት እስኪመለስ ሕይወት የሞት ማገዶ መሆኑ ይቀጥላል።

የወላድ ማህፀን በድባቡ ይኑርና የእናቶችም ዛሬ ቤዛ የሆነውን ጀግና የሚተካ ሌላ ጅግና ለነገው ትግል ይፀንሳሉ። በዚህ መልክ የተቀጣጠለው የትግል እሳት እንዳይዳፈን እናቶች የጦርነት ማገዶ አቅራቢነታቸውን ሙያየ ብለው እንዲወስዱት ይገደዳሉ። በመሆኑም ትግሉ ያለማቋረጥ ሕይወት እየበላ የቀጣይነት ዕድሜ ይኖረዋል። የትግሉ ቀጣይነት ዕድሜም እየረዘመ ሲሄድ ህዝቡ ሞትን እየሞተ መኖሩን ይለማመደዋል። ይልቁንም ሞት አስፈሪነቱ ቀርቶ የጅግነነት ዓርማ ይሆንና ልጆች አድገው እንደ ትልልቅ ወንድሞቻቸው ጀብዱ ሠርተው ለመሞት ጉጉት እንዲያድርባቸው ያደርጋቸዋል። በዚህ መልክ ብዙዎቹ ታዳጊ ወጣቶች ዕድሜ ዳ ሲልባቸው ገና በጧቱ የእሳት እራት እየሆኑ ማለቅን ይመርጣሉ። ለምን? ቢባል መኖር በራሱ ተስፋውን አጨልሞባቸዋልና!

የሕይወት ችቦም እንዲህ እንዲህ እያለ የነጻነት ቀንዲል ሆኖ ይኖራል። የፍልስጤም ጀግኖችና የነ ላይላ ካሊድ ዓርማ መሬት ነክቶ የማያውቀው በዚህ ምክንያት ነው። የወላዶች ማህፀን ጀግና መፀነሱን በቀጣይነት ስለያዘው በፍልስጤም የትግል ታሪክ ጀግና ይወለዳል እንጂ አይሞትም። ሺህ ጀግኖች ለፍልስጤም መብት ሰማዕት ሆነዋል። እንደ ትናንቱ ዛሬም … ነገም … መስዋዕት ይሆናሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአፍጋን ጀግኖችም ለቅኝ ገዥ አንንበረከክም ብለው ለአፍጋን ህዝብ ነፃነት ሕይወት ገብረዋል። እንደ ፍልስጤሞችና አፍጋኖችም ጎንደሮች ለህዝባቸው መብት ሰማዕት ሆነዋል። እየሆኑም ነው። ገናም ይሆናሉ።

ያልተቋረጠው የፍልስጤሞች ትግል በብዙ መልኩ ከጎንደሮች ትግል ጋር ተመሳሳይነት አለው። የፍልስጤማዊያን ትግል በዕድሜ ርዝመቱ ልቅና ይኑረው እንጂ በባህሪይው ግን ከጎንደሮች ትግል ጋር የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ ያለው ትግል ነው።

እስራኤላዊያንና ፍልስጤማዊያን ወንድማማቾች ናቸው። ትግራዊያንና ጎንደሮችም እንዲሁ። እስራኤሎችንና እና ፍልስጤሞችን ያጣላው የመሬት ጥያቄ ነው። የትግራዊያንና የጎንደሮች ጥልም መነሾው የመሬት ጥያቄ ነው። የፍልስጤሞች የዕምነት መሬት ምስራቅ ኢየሩሳሌም ስትሆን፣ የጎንደሮች የዕምነት መሬትም ዋልድባ ነው። የፍልስጤሞች የውኃ ጥያቄ የጆርዳን ወንዝ ሲሆን፣ የጎንደሮች የውኃ ጥያቄም የተከዜ ወንዝ ነው።

በፍልስጤምና በእስራኤል ጦርነት ጠብ አጫሪዋና ጉልበታሟ እስራኤል ስትሆን፤ በጎንደሮችና በትግራዊያን ጦርነትም ጉልበታሟና ጠብ አጫሪዋ ትግራይ ነች። በፍልስጤምና በእስራኤል ጠብ አልሞት ባይ ተጋዳዮቹ ፍልስጤሞች ሲሆኑ፤ በጎንደሮችና በትግራዊያን ጠብም አልሞት ባይ ተጋዳዮቹ ጎንደሮች ናቸው። የፍልስጤሞች ጥያቄ መፍትሔ ለማግኘት ዘመናት እንዳስቆጠረው የጎንደሮችም ጥያቄ እልባት እስኪያገኝ ዘመናት ማስቆጠሩ አይቀሬ ነው። ስለሆነም ጎንደሮች ፍልስጤሞችን ሆነዋል። እንዴት? ቢሉ የሁለቱም ህዝቦች ጥያቄ ማጠንጠኛው የማን መሬት? ሆኗልና!

እንደ ቀደምቱ ፍልስጤማውያን ጅግኖች የኛም አባቶቻች ክቡር ሕይወታቸውን ሰውተው ነው ባላገር አድርገውን የኖሩት። እንደ ህዝብ እንድንኖር፤ እንደ ሰውም ባላገር እንድንሆን አባቶቻችን የሕይወት ዋጋ ከፍለውልናል። እንደ ህዝብም እንድንኮራ ነፃነት አጎናጽፈውናል። ህዝብ ያለ ሀገር ህዝብ ሆኖ መኖር እንደማይችል፤ መሬትም ያለ ህዝብ ሀገር እንደማይባል ክቡር የሕይወት ዋጋ ከፍለው ታሪክ አስተምረውናል። አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ተንበርክኮ መገዛትን ሳይሆን ዕምቢኝ ለክብሬ፤ ዕምቢኝ ለሙብቴ፤ እምቢኝ ለነጻነቴ ብሎ ማመጽንና ገድሎ መሞትን በደም ቀለም ፅፈው የጀግነነት ታሪክ አውርሰውናል።

ሞትና ጀግንነት

ሰሜን ጃናሞራንና ጠለምትን ጎንደሬ አድርጎት የኖረው የነደጃች ውቤና የነአጥናፉ መሸሻ ጀግንነት ነበር። ወልቃይትን፤ ፀገዴን፤ አርማጭሆንና አዳኝ ሀገርን ጎንደሬ አድርጎት የኖረው የነቢትወደድ አዳነ መኮነን ጀብዱ፤ የነቀኛዝማች ገብሩ ገበረ መስቀል አይበገሬነት፣ የነራስ ውብነህ ነፍጠኝነት፤ የነደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋሪያት አርቆ አስተዋይነት፣ የነደጃች ብሬ ዘገየ ጀብዱ፣ የነደጃዝማች አስፋው ተሰማ፣ የነዳኘው ተሰማ፣ የነባላንባራስ አላባሽ በሪሁን፣ የነፊታውራሪ በረደድ አስፋው፣ የነገሪማ ታፈረ፣ የነፊታውራሪ አየለ አባ ጓዴ፤ የነረዳ ተሰማ ለጠላት አይበገሬነት ነበር።

የቀደምቱን ዓርማ አንስተው እነነጋ ነወጠ፤ እነሻለቃ አጣናው ዋሴ፤ እነአባ ታከለ፤ እነኪዳነ ማርያምና ሌሎቹም ... ነጻነት ሲገፈፍ ሞትን ይኖሩታል እንጂ አይሞቱትም በማለት ሞትን አቸንፈው የኖሩ ሰማዕታት ነበሩ።

ዛሬም የጎንደር እናቶች ማህፀናቸው አልደረቀም። ጀግና ይወለዳል እንጂ አይሞትም እንዲሉ እነ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱን ወልዷል። አዳዲስ አጣናው ዋሴዎች፤ አዳዲስ ኪዳነ ማርያሞች፤ አዳዲስ ነጋ ነወጠዎች፤ አዳዲስ አየለ አባ ጓዴዎች ተወልደዋል። እየተወለዱም ነው። የወላድ ማህፀን በድባቡ ይኑርና ገናም የላቁ ደመቀ ዘውዱዎች በሺህ ይወለዳሉ።

ሀገሬ አርማጭሆ ጀግና እንጂ ቡከን አያበቅልም። የወልቃይት ምድር ከጀግናም ጀግና መውለዱን ያውቅበታል። ሀገሬ ጋይንትና ደብረ ታቦር ዳግማዊ አድማሱ በላይን ፀንሷል። ስለሆነም ሞት ጎንደሮችን ይፈራል እንጂ ጎንደሮች ሞትን ከቶ ሊፈሩት አይችሉም።

ጎንደሮች ሞትን መኖር ከጀመሩ አርባ ሁለተኛውን ዓመት (1966-2008) ባለፈው ወርሃ ሚያዝያ አክብረዋል። ይህም በኢትዮጵያ የዕርስ በርስ ጦርነት ታሪክ ጎንደር ቀዳሚውን ስፍራ እንድትይዝ አድርጓታል። የጎንደሩ ረኸም የትግል ጉዞ የኤርትራውን ትግል "አጭር" አስመስሎታል። ዛሬ የዘመናችን አፋዓ ቤት የጎንደር ከተማ ሆናለች። የዘመናችን ናቅፋና ቃሮራም ወልቃይትና አርማጭሆ ሆነዋል።

ትናንት በኤርትራ መሬት እንደ ተመረተው ዛሬም በጎንደር መሬት የሚመረተው የሞት ሰብል ሆኗል። የሞት መኸር ከዋኝ የሆኑት ጎንደሮች ግን እንደ ኤርትራዊያን ወንድሞቻቸው ከሰላሳ አምስት ዓመት መራር ትግል በኋላ የጦርነት አውድማቸውን ጠራርገው ወደ ቤት የመመለስ እድል አልገጠማቸውም። ለምን? ቢባል ወያኔዎቹ የትግሬዎችንና የጎንደሮችን አበቃቀል የኢጋምና የቁልቋል አበቃቀል መልክ እንዲይዝ ስላደረጉት ኢጋሙም መውጋቱን፤ ቁልቋሉም መድማቱን አላቆመም።

ወያኔዎች ትግሬዎችንና ጎንደሮችን ኢጋምና ቁልቋል ማድረግ የጀመሩት ከአስራ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያዎቹ መባቻ ጀምሮ ነበር። ሀ ሲሉ 81 አዛውንት ጎንደሮችን ከወልቃይትና ፀገዴ ብሎም ድንበር ዘለው ከአምራኩባ (ሱዳን) እነፊታውራሪ አዲሱን አፍነው መዳረሻቸውን አጥፉ። በነርሱ ቤት አዛውንት ጎንደሮችን በማጥፋት ታሪክን ያጠፉ መስሏቸው ነበር። አዛውንቱ ሲታፈኑና መዳረሻቸው ሲጠፋ ግን የወልቃይት ህዝብ አልተንበረከከም። ይልቁንም ወጣቱ ወልቃይቴ የታፈኑ አባቶቹን ዓርማ አንስቶ የማን መሬት? ብሎ ጠየቀ። ከሦስት ሺህ በላይ ወጣቶችም በጥያቄው ሳቢያ ወደ ትግራይ ተወስደው መዳረሻቸው ጠፍቶ ቀረ። ቀሪው ወልቃይቴም በገዛ ሀገሩ ስደተኛ እንዲሆን ተፈረደበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉም የጎንደር ካህናት የወያኔ የፖለቲካ ሰለባ እንዲሆኑ አዲስ የድራማ መድረክ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ተጀመረ። ድርጊቱ ካህናቱን እንቅልፍ ነሳ። ቁስ በስቀሉ ምዕመን በቃሉ የወያኔን እብሪት አወገዘ። ለምን ተደፈርን ያሉት ወያኔዎችም ጳጉሜ አንድ 1984 ዓ.ም. “ወጣቶችን ለአመፅ እያዘጋጀህ ነው” በሚል ሰበብ ባህታዊ አምሃየስን ለማሰር ጎንደር ከተማ ውስጥ በቀሰቀሱት ግርግር ከሰላሳ ያላነሱ መዕመናን አደባባይ ኢየሱስ ላይ ተጨፈጨፉ። ባህታዊ አምሃየስን ጨምሮ ከአምስት መቶ በላይ ምዕመናን እየተደበደቡ እስር ቤት ተጎደጎዱ። ባህታዊውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከአዲስ አበባ እንዳይወጡ ተከልክለው የቁም እስረኛ በመሆን አስራ ሦስተኛ ዓመታቸውን አስቆጠሩ።

በግርግሩ ሰሞን አደባባይ ኢየሱስ ላይ በተካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ መምህር መንክር “ደግሞ እንደ መሬቱ ዕምነቴንስ አላስወርስም” ሲሉ በዕምነታቸው ፀንተው ስለቆሙ ከእስር እንደ ተፈቱ በመድኃኒት ተገደሉ። ሞታቸውን ተከትሎም፡-

ቀና ብየ ሳየው ሰማዩ ቀለለኝ

ደግሞ እንደ ሁመራ ደግሞ እንደ ጠገዴ

የዕምነት መስቀሉንም ወሰዱት መሰለኝ፣

ስትል አንዲት አስለቃሽ ሙሾ ደረደረች። በደሉ ግን በዚህ ሙሾ አልተቋጨም። በቀጣዩ ዓመት መስከረም/ጥቅምት ወር ላይ የሱዳን ተወላጆች በወታደር ታጅበው ቋራ ድረስ ዘልቀው የቅርቅሃውን ደን ሲጨፈጭፉ ድንበሩን ለመታደግ የወጣው ገበሬ በሱዳን ወታደር ከፍተኛ ጥቃት ደረሰበት። የወያኔ ወታደር ግን ይበላችሁ ለማለት ይመስላል፤ በቅርብ እርቀት ቆሞ ጥቃቱን ይመለከት ነበር። ይህን ሀገራዊ ክህደት አስመልክተው ገበሬዎቹ አገዛዙን ስለተቹ በጥይት ተደብድበው አለቁ።

ያ እልቂት ከ 13 ዓመት ቆይታ በኋላ ሰሞኑን ተደገመ። ለ 13 ዓመት ደመና አርግዞ የኖረው የጎንደር ሰማይ የደም ዝናቡን ሰሞኑን ጣለ። በዚህ የበደል ዳፋም የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት ጎንደሮች ፍልስጤምን ሲሆኑ፤ እንደገና ጎልተው ታዩ። የትግሬዎች ፂዎናዊነትም ነጥሮ ወጣ ። የጎንደሮች የማን መሬት? ጥያቄ ግን አየር ላይ ተንጠልጥሎ ስለቀረ ትግሉ ይቀጥላል።

ሐምሌ 2008

አብርሃም በየነ (aderaj3106@gmail.com)

EMF